# የዕርዳታና የድጋፍ ማሰባሰቢያ ጥሪ

የሀገር ጉዳይ ይመለከተናል ለምትሉ ወገኖቻችን ሁሉ

አማራው ነፃነቱንና መብቱን ለማስከበር እራሱን የትግራይ ነፃ አውጪ ነኝ ከሚል ዘረኛና እብሪተኛ ቡድን ጋር በገጠመው ትንቅንቅ እየተዋደቀ የሚገኝ ቢሆንም ትግሉ ግቡን እስኪመታ ቀጣይ ነውና የኛም የወገኖቹ ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ ተፈላጊ መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም

በመሆኑም ይህን አገር የማዳን ጥሪ አሁንም እንደገና ያቀረብንበት ምክኒያት ትግሉ ውጣ ውረድ የበዛበትና እልህ አስጨራሽ ቢሆንም ቀሪው ምርጫ ባርነት ብቻ ስለሚሆን ለነፃነታችን ከሚዋደቁ አርበኞቻችንና ከቀሪው ወገናችን ጎን የመቆም አገራዊም ሆነ ወገናዊ ሃላፊነቱ እኛም አለብን ብለን ስለምናምን ነው

ግባችንም ለዚህ ጦርነት ለታወጀበት ወገናችን አጋር በመሆን በቀጣይነት ለችግሮቹ በመድረስ ዕርዳታ እንዲደርሰው ማድረግና በውስጥም በውጭም የአማራውን የታፈኑ ድምጾችም ሆነ ጩኸቶች ለማሰማት ይረዳ ዘንድ ለማቋቋም በዕቅድ ተይዞ የነበረው ሞረሽ ወገኔ አማራ ራዲዮ በእናንተም አስተዋጽኦ ጭምር ኦክቶበር 1/2016 ዓም የሙከራ መርሃ ግብሩን አየር ላይ በማዋል ሥራውን ጀምሯልና እነዚህንና ሌሎች አስፈላጊ ወጭዎችን ለመሸፈን የሚየስችል የገንዘብ ዕርዳታ ማሰባሰብ ነው

በስብሰባችንም ላይ የሞረሽ ወገኔ ዓለም አቀፍ ሊቀ መንበር አቶ ተክሌ ይሻው ዕርዳታ ለማሰባሰብና ሞረሽ ወገኔ ያሳተመውን (ምጽአተ ዐማራ) መጽሐፍ ለማስመረቅ በተያዘላቸው መርሃ ግብር መሰረት በተለያዩ ዓላማት በመዘዋወር በስብሰባው ከታደሙ ወገኖች ጋር ውይይት የማድረግና ሃሳብ የመለዋወጥ ዘመቻ ኦክቶበር 27 2016 በዋሽንግተን ዲሲ የጀመሩትን ጉዞ በመቀጠል ኖቬምበር 5 2016 ቅዳሜ ደግሞ ተራው የስዊድን በመሆኑ በስቶክሆልም እመካከላችን ይገኛሉ

እርሰዎም በቀኑና በሰዓቱ በቦታው በመገኘት የበኩለወን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለነፃነታችን በሚዋደቀው ወገናችን ሥም ጥሪ አቅርበንለዎታል

የስብሰባው መርሃ ግብሮች

1. የሞረሽ ወገኔ ስዊድን ሰብሳቢ ወሮ ዘውዲቱ የማነ ታዳሚውን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት የዕለቱን የክብር ዕንግዳና የስብሰባውን መርሃ ግብሮች በማስተዋወቅ መድረኩን ይከፍታሉ

2. አቶ ተክሌ የሻው የዓለም አቀፍ ሞረሽ ወገኔ ሊቀ መንበር ንግግር ያደርጋሉ

3. ታዳሚው ከቶ ተክሌ ጋር የሚደረግ ውይይትና የጥያቄና መልስ ጊዜ ይኖረዋል

4. ሞረሽ ወገኔ ያሳተመው "ምጽአተ ዐማራ" መጽሐፍ ምረቃ

5. የእራትና የዕርዳታ ገንዘብ ማሰባሰቢያ ጊዜ

ቀን **2016 - 11 - 05**

ሰዓት **13:00 - 22:00**

ቦታ **Hjalmarsvägen 28**

**120 53 Årsta**

**ከአክብሮት ሰላምታ ጋር**

**ሞረሽ ወገኔ ስዊድን**